# ለቅምሻ

*ሐዋርያ ቅጽ 15፣ ቁ 8 የካቲት 2002 (February, 2010)*

*የተከበራችሁ አንባቢያን፡ ከአዲሱ የየካቲት 2002 (ፌብሩዋሪ 2010) የሃዋርያ እትም ለቅምሻ ያህል ከተወሰኑት ዝግጅቶች ላይ ቆንጠር ቆንጠር አርገን እነሆ አቀረብንላችሁ። ሙሉው እትም ለሐዋርያ ደንበኞቻችን አስኪደርስና ቀደሚታ እድል እስኪያገኙ ድረስ ለሁሉም ከመቅረብ ይታቀባል። እንግዲህ በሁዋላ የሐዋርያን እትም እፍታ በወቅቱ እንዲደርሳችሁ የምትፈልጉ ሁሉ የየራሳችሁን ቅጅ እንድታዙ እናሳስባለን።*

*ማዘዝ ለምትሹ ሁሉ አድራሻችን እነሆ፣*

Hawarya.publications@sympatico.ca

Website: www.hawarya.net

*ከምስጋን አጋር*

*ከሐዋርያ ዝግጅት ክፍል*

//////// ………/////////

## ለዓውደ ሃሳብ ዓምድ፤

"በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ሥልጣን መጋራት እንደ አማራጭ ሊታይ ይችላል ወይም አይችልም የሚለውን አሻሚ ጥያቄ በቅጡ ለመመለስ፡ በእኔ አስተያየት በቅድሚያ በንድፈ አሳብ ደረጃ ሥልጣን መጋራት ምን ማለት እንደሆነና፡ ለምን አላማና ግብ፡ በእንዴት ያለ ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል መመርመሩ ግንዛቤ ያስጨብጣል ብዬ አስባለሁ። ከዚህ በተጨማሪ በዴሞክራሲና በአምባገነን ሥርዓት መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት ይጠቅማል። በአንባገነን ሥርዓት ውስጥ አንድ ፓርቲ በጉልበት የራሱን ሕግ መንግሥት ደንግጎ የሕዝብን የዴሞክራሲያዊና የስብአዊ መብቶች አፍኖና ረግጠው የሚገዛ ሲሆን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚገኙ ብዙሃን የፓለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ተወዳድረው አሸናፊው ፓርቲ ሕገ መንግስቱ በሚፈቅደው መስረት ለተወስነ ጊዜ የሕዝብን አገልጋይ ይሆናል ማለት ነው። በማያሻማ መንገድ ሕዝባዊ መንግስት ነው። በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ከሚገኙ አገሮች መካከል ያንዳንድ አገሮች ተመክሮ ማለት የሥልጣን መጋራት ሊከስት በሚችልበት በፓርላሜንትሪ ዴሞክራሲና በቀይጥ ማለት የፓርላሜንተሪና ሕገ መንግሥታዊ ዴሞክራሲ የሚገለገሉ እንደ ጀርመን፡ እስራዔልና ጃፓን ወዘተ.. ማጥናቱ ይበጃል ባይ ነኝ። ስለ አምባገነን ሥርዓት ብዙም ሩቅ መሄድ የሚያስፈልግ አይመስለኝም፡ ሁላችሁም እንደምታውቁት የአፍሪቃ ቀንድ አገሮችና መሪዎች በቀውስ የሚናጡት በቂ ማስረጃዎች ናቸው። የሥልጣን የመጋራትን ጉዳይ በጥልቀት ለመረዳት ማለት የዴሞክራሲ ሥርዓት ያላቸው አገሮችና የዴሞክራሲ ሥርዓት የሌለባቸው አገሮች ብሎ በሁለት ከፍሎ ማየቱ ከውኸምብር የፃዳ አስተሳስብ ሊያስጨብጥ ይችላል የሚል ግምት አለኝ። ..----" ከአበበ ዋሲሁን

.////////////…../////////////

## ለዓውደ ሃሳብ ዓምድ፤

"ጥያቄ፦ በ"ድህረ-ህዋ' መገናኛ (ኢንተርኔት) 'የፖለቲካ ቨረንዳ አዳሪ" (political homeless) የሚል አዲስ ሃረግ ብቅ ብሉዋል፡ ግንዛቤው ምን ማለት እንደሆን ማብራራት ይቻላል?

*መልስ፤ አገላለጹ አዲስ ባይሆንም አንዳንድ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ላሉበት ሁኔታ መገለጫ ይሆን ዘንድ በአማርኛችን ተከሽኖ መቅረቡ የሚከፋ አይደለም። 'የፖለቲካ ቨረንዳ አዳሪ' የሚለው አገላለጽ "political bankruptcy" (የፖለቲካ ድህነት) ከሚለው የእንግሊዝኛው አገላለጽ የተለየ አይሆንም። የፖለቲካ ድህነት ለአንድ የፖለቲካ ስብስብ (ፓርቲ፣ ቡድን) ወይም ግለሰብ በተለያዩ ሁኔታዎችና መንገዶች ሊገለጡበት የሚችል ቢሆንም በዋናነት ግን መርህ አድርጎ የያዘውን አቅዋም ሲያውገረግርና አድርባይነት ሲጠናወተው የሚከሰት ነው። በአማርኛችን አገላለጽ "የፖለቲካ ቨረንዳ አዳሪ" የተባለው ምናልባት በአገላለጡ ብስለት ላቅ ብሎ ለሆነ ምክንያትና ጥቅም የፖለቲካ መተክላቸውን ያውገረገሩና ጥያቄ ውስጥ ያስገቡ የፖለቲካ ክስተቶች ከሁለቱም ሳይሆኑ መና መቅረታቸውን ሊያመላክት ይችላል። ይህ ሃቅ ደግሞ በትክክልም በቅርቡ የፖለቲካ ታሪካችን እንደ ግለሰብም እንደ ስብስብም አንዳንዶቹን አግጥሙዋቸው ሲማስኑበት የምናየው ነው። ለሆነ ስሌት ከነበሩበት ድርጅት ሰንካላ ምክንያት ፈጥረው ወይም "አዲስ ቅኝት" አነብንበው በመውጣት፣ ወይም ደግሞ እጥፍ ብለው በማደርና የተለየ አቋዋም በመያዝ እንቅስቃሴያቸውን ወይም ግላዊ ጥቅማቸውን ለማራመድ ያለሙ ክፍሎች እንዳሰቡት ሳይሆንላቸው ቀርቶ ሜዳ ላይ አጉዋጉል መሆናቸውን በትዝብት ተመልክተናል፣ይህ አይነቱ ባህርይ ለሀገር አቀፉ ግስጋሴ ምንኛ ጎታችና ጎጅ እንደሆነም ከተግባራዊ ውጤቱ እያስተዋልነው ነው። የፖለቲካ ድህነት ብሎም የፖለቲካ ቨረንዳ አዳሪነት ከቁጥጥር ውጭ በሆነ ችግር ምክንያት የሚከሰት ገጠመኝ ሳይሆን፣ በግለሰቦች የተሳሳተ ስሌት ተመርቶ መውጫም ሆነ መመለሻ ወደሌለው አቅጣጫ የሚያመራ የአስተሳሰብ መሃንነት ነው። .."*

*ፈዲሉ አሚር (ከአውሮፓ)*

////////////////// ..../////////////////////////

*ለዓውደ ሃሳብ ዓምድ፤*

ጥያቄ- ሽብርን በአሸባሪ ሃይል መከላከል ወይም ማሸነፍ ይቻላል? ሽብርና አሸባሪ እንዲጠፉ ብልሃቱ ምን ይሆን?

*"መልስ- ለዚህ መንታ ጥያቄ ቋት የሚሞላ መልስ ኖሮኝ ሳይሆን የወቅቱን የፕሮፖጋንዳ መድረኮች ያጣበበና ሲተገበርም እጅግ አወዛጋቢ በመሆኑ መነሳት ያለበት ጉዳይ ነው በሚል አዎንታየን ለመግለፅ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ይህ "ሺብር" የሚለውና የፈረደበት ቃል ትርጉሙ ምንድን ነው?*

*ሜሪያን ዌብስተር መዝገበ ቃላት "ፍርሃት ማሳደር" "ጭካኔ" "ዓረመኔ" "ነብሰ በላ" "ስርዓት ያጣ" "ጭንቅ" (ትርጉሙ የራሴ) የመሳሰሉትን ያስቀምጣል። ሆኖም ግን ሺብርተኛና ሺብርተኝነት ሲባል የድርጊቱን ባለቤትና የድርጊቱን አፈፃፀም ገላጭ ይሆንና ስርዓት የሌለውና ጅምላ ግድያ፣ ጭፍን ሃይል በመጠቀም ፍላጎትን ማስፈፀም፣ የጌስታፖ እርድ አንቀትቅጥን በመጠቀም ብቸኛ ፍላጎትን በግለሰብ፣ በቡድንና በሕብረተሰብ ላይ መጫን የመሳሰሉትን ይጠቁማል። ለምሳሌ አሰቃቂ የአካል ድብደባንና የስነ-ልቦና ጭንቀትን በማሳደር (ቶርቸርን በመጠቀም) ሚስጥር ለማግኘት መሞከር፤ ከግለሰብ እስከ ሕብረተሰብ ባሉት ላይ ጅምላ ግድያንና እስራትን በማካሄድ በፍርሃት እንዲገዙ መጣር፣ ታዋቂ በሆኑ ግለሰቦች ላይ ግድያን (አሳስኔሺን) በማካሄድ አቅጣጫን ለግል ጥቅም ማስቀየር ወዘተ ይገኙበታል። ..." ከይልቃል ጀንበሩ (ከአሜሪካ)*

///////////////////……/////////////

"ከላይ በመንደርደሪያዬ "ቅዝቃዜውን" በተመለከተ የዘንድሮውን የከፋ ብርድ አውሮፓና አሜሪካ ስንቆዝመው የሩሲያኑን የክሬምሊን አበጋዝ "ብላድሚር ፑቲንን" ያስታውሰናል። አምናና አቻምና ብዙዎቹ የኢዥያና የምስራቅ አውሮፓ ሀገሮች "በቁርጥማት" ሲታሹ ከርመው "እትቱ...!በረደን..!"ሲሉ ሰንብተው ነበር። ነፍጠኛው (ብሄርተኛው) መሪ "ብላድሚር ፑቲን" የጋዝ ዕቀባ በአጎራባች ሀገሮች ላይ ጥለው ከፊሎቹ በየመድረኩ ሲንጫጩ ተደምጠው ነበር። ውልና ግዴታቸውን ሳይወጡ ሲቀር ነፍሳቸውን አይማረውና የቀድሞው የኬጂቢ አበጋዝ "ሚስተር ፑቲን" የጋዝ ቦንቦውን ደፍነው (ዘግተው) አጎራባች ሀገሮችን መቸም "ጉድ" ሠሩዋቸው!! የምን ጉድ..? ብትሉ፡ ዕቀባ ነዋ..!! "ዕቀባ" ታዲያ ፍቱን መድሃኒት ነው።

በዲፕሎማሲው ዓለም ባላንጋራን ሀገር፡ አለ አይደል ..? የፈጢኝ አስሮ "ለማሸት" የምት ምት አለው። በሌላ በኩል አውሮፓዊያኑና አሜሪካዊያኑ በሞኖፓል በሚቆጣጠሩት የዓለማችን የመገናኛ ብዙሃን "ዕቀባ" ..! ዕቀባ …!" ቢሉም በተዘዋዋሪ ግን ደግሞ የጦር መሳሪያዎቻቸውን የኢኮኖሚ ፍጆታቸውን በሚስጥር ግን መቸብቸባቸው አቀይቀሬ ነው። .."
**"ዕቁብና ዕቀባ በኤርትራ"**

<u>ከሚለው የሚካኤል ምስግና (ስዊድን) ምጸታዊ ወግ የተቀነጨበ</u>

////////////////////// …///////////////////////

"ሶሶት ሰው ምስጢር የሚጠብቀው ሁለቱ ከሞቱ ነው ( ሀፓና ሲሪ ያ ዋቱ ዋዊሊ) የሚል የኬንያ ተረት አለ፤ ከመሞት በመለስ ምስጢራችንን ይዘን መቆየት መቻል ሲገባ ለወያኔውም ሰርጎገብ፤ለቅጥረኛው ጆሮ ጠቢም ሆነ ሰላይ፤ ለእበላ ባዩና ይህን ካላዋረሁማ ለልሙት ባዮች ሁሉ ሰለባ ሆነን የትግሉ ገበናና ምስጢር በአደባባይ መሰጣቱ አልቀረም። ይህ ሆኖ እያለ አላይምን መመሪያ አድርገው ከወያኔ የቀረውን ወይ ያመለጠውን አፋችንን ሊለጉሙን የተነሱ አሉ። ከንቱ ልፋት!

ሃባሪ ወንድም እህቶቼ እንደገና። በወር ውስጥ ነገሮች ተባባሱ ተበላሹ እንጂ አልተሻሻሉም። ህጋዊ ድርጅቶች ከወያኔ የሥነ ሥርዓት ስምምነት ተፈራረሙ ቢባልም ይህ አፈና የለመደ ቡድን በርካታ ዜጎችን ማሰርና ማሰቃየቱን አላቆመም…" ከዜናው ባሻገር የመስፍን ታምራት አምድ የተቀነጨበ

////////////////////////////////// …..//////////////////////////////////



"ኢትይጵያ በመልካም ሁኔት ከአንድ አስከፊ መልክ ወደ ጥሩ ዘመን ለመሸጋገር ብቁ ናት። ይኽ ደግሞ የሕዝቡ የረጅም ጊዜ ትዕግስቱ የወለደው ፍሬ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይገባል። ዳሩ ግን፣ የዚህ ዘለቄታ የሚቻል ሲሆን፣ ከሕዝብ አቅምና ቁጥጥር ውጭ የሚሆኑ ሁኔታዎች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ሳይገመት የሚቀር አይደለም። ኢትዮጵያ ሆነ ተብሎ ከተፈጠረላት አሁን ካለችበት ሰፊ ውዝግብ በተረጋጋ መልክ እንድትሸጋገር ለማድረግ የሕዝቡና ያሉት መሪዎቹን የጠበቀ ብልህነትን ይጠይቃል። በዙሪያዋ ያሰፈሰፉ ከባድ አጥፊዎች የሰፈሩበት ሁኔታ ይታያል። ከዚሁ ወጥንቅጥ የሚጠቀሙ የወዳጅ ጠላቶችም እንዲሁ ወቅቱን ይጠብቃሉ። ይህን የኢትዮጵያ ሕዝብ አጥብቆ ይረዳል። ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የጥያቄ መልሶች ጥሩ፣ ጥሩ ሁኔታዎችንና በጎ ድርጊቶችን በማብጣጠም ነው። ዳሩ ግን፣ የተሰጡት ትንትኖች መልካቸውን ሊቀይሩ የሚችሉበት ሌላ ግጭቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። በዕውነቱ ከሆነ ዘለቄታን ለማምግም አስቸጋሪ ነው። ብዙ የሚይታወቁ መልኩን የሚለወጡ ድርጊቶች ሊመጣ ጩ ሊፈጠሩ ስለሚችሉ ነው። ስለዚህ፣ ማንም ሰው የበጎውን ኃይልና የብልህ አስተሳሰብን አስመርኩዞ የቀና ዘለቄታ ቢያስብም፤ ሌላውንም አስቸጋሪ ዘለቄታ አመዛዝኖ ማቅረብ ይኖርበታል። …" ዘወግ ፋንታ ለአእወደ ሃሳብ ዓምድ ጥያቄዎች መልስ ካቀረበው ሰፊ የመልስ ማብራሪያ የተወሰደ

//////////………..//////////

"በአፍሪቃ የጦርነት ታሪክ ሁለት የተከበሩና የተደነቁ ጦርነቶች አሉ። በህኒባል መሪነት አፍሪቃዉያን አውሮፓውያንን ድል ያረጉበት ሲሆን ሁለተኛው ኢትዮጵያውን በአድዋ ጦርነት ጣሊያንን ድባቅ የመቱበት አንፀባራቂ ድል ነው። ባለንበት ዘመን የኢትዮጵያ አኩሪ ታሪክና የህዝቧ የአትንኩኝ ባይነትና የአርበኝነት መንፈሳዊ ቅርስ እጅግ በጣም አሳሳቢ ፈተና ውስጥ ገብተዋል። የአድዋ አኩሪና አንፀባራቂ ድል፡ የአጤ ምኒልክ አስባሳቢ፡ አርቆ አሳቢና ይቅርባይ የአመራር ስልት ለዛሬው ትውልድ ወቅታዊነቱና አራያነቱ የጎላ ነው።…የእናት አገራችን የኢትዮጵያ ችግር አገራዊና ህዝባዊ የአርበኝነት ቅርሷን በተከታታይና በአስተማማኝ ሁኔታ ለሚቀጠለው ትውልድ ማስላለፍ ያለመቻል ነው። አኩሪው አገራዊና ሕዝባዊ የታሪክ ቅርሳችን እንደሚያሳየን አጤ ቴዎድሮስ፡ በጠላት በመማረክ የአገራቸውን የኢትዮጵያንና የህዝቧን ክብር ከማዋረድ ሞትን በመምረጥ ሽጉጣቸውን ጠጥተው ህያው የተጋድሎና

የመስዉእትነት የታሪክ ቅርስ አወረሱን። አጤ ዮሐንስ ደማቸውን በመተማ ኢትዮጵያ ድንበር ላይ አፍስው በመንፈስ ጽኑ ተከታይቸው አደረጉን። የቁርጥ ቀን የኢትዮጵያ ልጅ  ዘረአይድረስ በሮም አደባባይ የኢትዮጵያን ታሪክ አስከበረ። ጅግናው አብዲሳ አጋ በአውሮፓ ምድር ፋሺስትን በመቅጣት አርአያ ሆነን።.."

*ለአድዋ ጦርነት አንፀባራቂ ድል፣ ለ113ኛ ዓመት መታሰቢያ ሻለቃ ግርማ ይልማ ቡልቡላ ካዘጋጁት ጣፋጭ ዝግጅት የወሰደ፤*

//////////////.../////////////////

" "የሚሆነው ይሆናል አትጨነቁ" የሚል ግብዝ ብሂል አለ። ሃቁ ግን የማይሆነውም ሆኖ  የማየቱ ሃኬት ነው። አንዲያው ለጨዋታው ሲባል "የሚሆነው ይሆናል" ቢባልም፣ የመና መስኮቶች በየትየሌሌ አውቆ ግብር (አቶማቲክ) ዕደ-ጥበባዊ ክንዋኔ ክፍት ዘጋ እያሉ መንፈሳዊ እርካታም ይሁን ቁሳዊ ፋይዳ አይናኙም። "ጥረህ ግረህ ብላ፣ አንኩዋኩ ይከፈትላችሁዋል" ተባለ እንጅ፡ እጅና እግራችሁን አጣምራችሁ "ይሆናል"ን ጠብቁ አልተባለም። እናም መንፈሳዊ እርካታችንንና ቁሳዊ ፍላጎታችንን ከደመ-ሥጋችን ጠብ በምትል ላባችን ልናገኛት ዘውትር እንጣር ነው መልእክታችን።

"ሐዋርያ" ብለን ከአድማስ አድማስ መሻገር የቻለቺውን ጋዜጣችን ማሰራጨት ስንጀምር፣ ዓላማችን እኛ የኢትዮጵያ ልጆች በቁዋንቁዋችን ስለዕለት እንጀራችንና መጣዒ ተስፋችን መነጋገርና መግባባት አንችል ዘንድ የበኩላችንን "አንዲት ቀለም አለላ" አስተዋጽኦ ለማበርከት ነው። "ነብር ዥንጉርጉርነቱን፡ ኢትዮጵያዊ መልኩን መለወጥ ይቻለዋልን?" የሚል አቢይ መለኮታዊ አንደምታ ገና ድሮ ተሰጦናል፤ በመልካችንና በባህርያችን ግርማ ተለይተንም የተጨነቁ የሰው ልጆች መጠለያና ዋስትና ያገኙ ዘንድ  "ወደ ኢትዮጵያ ሂዱ" ተብለው በክብር እንግዳነት ተመርተውብናል። አባቶቻችንና እናቶቻችን በአድራጎታቸውና በእምነታቸው አላሳፈሩንም፤ አይከፍሉ እዳና መስዋእውትነት ከፍለው ባህርያዊ መልካቸውንም ሆነ እምነታቸውን ጠብቀው የማይሆነው እንዳይሆን በመጣር መሆን የሚገባው እንዲሆን አስችለዋል። "የሚሆነው ይሆናል" በሚል ብኩን አባዜ ሳይዘለሉ፣ በፈተናቸው ክብደት ሳይሰላቹና ተስፋ ሳይቆርጡ በአጭር ታጥቀው በጊዜ የሞሉዋትን ጽዋ ለጥዋት ተረካቢው ትውልድ አስተላልፈዋል። ተረካቢዎቹ ደግሞ እኛው ነንና ያስረከቡንን ሃላፊነት በአግባቡ ተቀብለን በመጠቀምና የጎደለውን ሞልተን እጅ እጃችን ለሚያየን አዲስ ትውልድ የማስረከቡ ሃላፊነት በእኛው ላይ ወድቁዋል። የተረከብናት ጽዋ የአባት/እናትን አደራ ሰፍራ የሞላች ናትና በጥንቃቄና በእንክብካቤ ካልያዝናት ክንብል ደፋ ልትል እንደምትችል ደግሞ መገንዘብ ያስፈልጋል፤ ጉዳያችን "ይታደሉታል እንጅ አይታገሉትም" የሚለው ሳይሆን፣ ይልቁንስ "ይታገሉታል እንጅ አይታደሉትም" የሚለው ተቃርኖ ነው። የጋራ ታሪክም ይሁን ግለሰባዊ ስኬታማ ህይወት ማጠንጠኛው ጥረትና ግረት ነው፣ የማያቋዋርጥ ተወራራሽነትና ቀጣይነት ያለው የጋራ ትግል የሕዝብንና የሀገርን ሉአላዊነት አስከብሮ ኑሩዋል። "መቀመጥ ቁምጥና ነው" ይለዋል ብሂላችን። ቁምጥና እንደማንኛውም ቅስም ሰባሪ በሽታ አሳፋሪ እንደመሆኑ መጠን፣ ተይዘን ከመማቀቃችን በፊት አስቀድመን እንጠንቀቅ ይረዳ ዘንድ የብሂሉ ትምህርታዊ ይዘት ጥልቅ ነው። .." "የማይሆነው እንዳይሆን" ከሚለው የሐዋርያ ርእሰ አንቀጽ የተወሰደ

///////////////////    ............//////////////////////

ክቡራትና አቡራን ወገኖች፡

አባካችሁ ተሳተፉ። ጋዜጣዋን በማዘዝ፣ ለአምድ የሚበቁ ጽሁፎችን በማበርከትን የማስታወቂያ ቦታ ገጽ በመግዛት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ልታደርጉ ትችላላችሁ። አምሳ ሎሚ ለአምሳ ሰው ጌጡ ነው..." የሚለውን ወጋችን እናስታውስ። ሊያጠናክረን የሚችል ትችታችሁና አስተያየታችሁም አይለየን። ለሚቀጥለው እትማችን ጥያቄዎችንና በዚህ እትም ለቀረቡት መልሶች አስተያየቶቻችሁን ላኩልን።

እስካሁን ትብብራችሁ ላልተለየን ወገኖች ሁሉ የከበረ ምስጋናችን ይድረሳችሁ።

ከዝግጅት ክፍል

Hawarya.publications@sympatico.ca

www.hawarya.net

Tel.  416-416-459-5964